## የኖቬምበር 2014 QuickNotes 1ኛ ዜና መልእክት

### የበላይ ተቆጣጣሪ ሶስተኛውን አመታዊ የMCPS ት/ቤቶች ይዘት ዲስኩር ያቀርባል

ኖቬ. 11 በስታራትሙር የሙዚቃ ማእከል የSuperintendent Joshua Starr ስለ ሶስተኛው አመታዊ የት/ቤቶች ይዘት ዲስኩር ከ600 በላይ ሰዎች ተገኝተው ነበር። ድርጊቱ የMCPS ማህበረሰብ አብረው በመሰባሰብ የMCPS ተማሪዎችን ፍፃሜዎችንና ክሂሎቶችን እንዲያከብሩ እንዲሁም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ስኬት ዲስትሪክቱ ሁሉን ተማሪዎች እንዴት እያዘጋጀ እንደሆነ የDr. Starrን ራዕይ ለመስማት አስችሏል።

ከንግግሩ በፊት፣ እንግዶች በMCPS ተማሪዎች በተዘጋጁ ድንቅ ሙዚቃና ውዝዋዜ ተዝናንተዋል፣ እናም የተማሪዎችን ኪነ-ጥበባዊ ስራ ለማየት ዕድል አግኝተዋል። በክውነቱ ከ100 በላይ ተማሪዎች በደርዘኖች ከሚቆጠሩ የMCPS ት/ቤቶች ተሳትፈዋል።

የ2014 የት/ቤቶች ይዘት ክውነት ሊካሄድ የቻለው በስትራዝሞር እና በግሌንስቶን ድጋፍ ነው። የእነርሱ ድጋፍ እነዚህ ድርጅቶች ከMCPS ጋር የነበራቸውን ሽርክና የሚያጠንክር ነው። የሙዚቃ ማእከሉ በ2005 ከተከፈተ ወዲህ፣ የስትራትሙር የተማሪዎች የሙዚቃ አቅርቦት ተከታታይ ትርኢት (Strathmore Student Concert Series) በሺዎች ለሚቆጠሩ የMCPS ተማሪዎች የሙዚቃ በአል አቅርቧል። ግሊንስቶን ከዲስትርክቱ ጋር ሽርክና የጀመረው በ2011 ሲሆን በመቶዎች የሚቆጠሩ መምህራንና ተማሪዎች ሙዚየሙን እንዲጎበኙ እና በአገሪቱ በጣም የታወቁ ዘመናዊ ኪነ-ጥበብ ስብስቦችን ለማየት አስችሏል።

የ2014 የት/ቤቶች ይዘት ክውነት ሊከናወን የተቻለው በተጨማሪ ከሽርኮች በተደረገ ስጦታዎች አማካይነት ሲሆን የሚያካትተውም፡-Educational Systems Federal Credit Union (የትምህርታዊ ስርአት ፌደራል የክሬዲት ማህበር)፣ Hess Construction + Engineering፣ Comcast፣ Discovery Education፣ International Baccalaureate፣ እና የMontgomery County Business Roundtable for Education (የቢዚነስ ጠረጴዛ ዙርያ ለትምህርት)።

ከድርጊቱ የተገኙ ገቢዎች ሁሉ የMontgomery County Public Schools Educational Foundation ተልዕኮ ለመደገፍ የሚያገለግሉ ሲሆን በተለይም Achieving Collegate Excellence and Success (በኮሌጅ ጥሩ ችሎታና ስኬት ማግኘት) (ACES) ፕሮግራምን ነው።

የACES ፕሮግራም የMCPS፣ Montgomery College እና በShady Grove የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል በከፍተኛ ትምህርት በብቃት ያልተወከሉ/የማይታዩ ተማሪዎችን ኮሌጅ ምዝገባና ጨርሶ መመረቅ ለማሻሻል የተቋቋመ የትብብሮች ጥርት ነው።

በACES ድርጣብያ ይበልጥ ተማሩ።

የክውነቱ ቪድዮዎችና ፎቶዎች በየት/ቤቶች ይዘት ድርጣብያ ተለጥፈዋል።

## Superintendent ለት/ቤት ህንፃ መስርያ በጀት $220.8 ሚሊዮን ጭማሪ ይጠይቃል

Superintendent Joshua P. Starr በMCPS ጎልቶ ለሚታየውን የቦታ እጥረት ለመፍታት ዲስትሪክቱ ታያይዞት በሚገኘው የስድስት አመት የት/ቤት ህንፃ ስራ እቅድ $220.8 ሚልሊዮን እንዲጨመር በመጠየቅ ላይ ይገኛል።

አብዛኛዎች ተጨማሪ ገንዘቦች ከስቴቱ ተጠይቀው የነበሩ ተጨመሪ የህንፃ ገንዘቦች ባለመገኘታቸው የዘገዩ በግዜ መስመር/በሂደት ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች መልሰው ይገነባሉ። ተጨማሪዎቹ የስቴት ገንዘብ በሚመጣው፣ ጃኑዋሪ በሚጀምረው፣ የሜሪላንድ ስቴት የህግ ምክር ቤት ስብሰባ እንደሚያልፍ Dr. Starr ተስፋ ያደርጋል።

በMontgomery County Council (ምክር ቤት) በሜይ ወር የቀረቡት ማሻሻያዎች የ2015-2020 Fiscal Year (የበጀት አመት) (FY) Capital Improvements Program (ካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም) (CIP) በጀትን ከ$1.53 ቢልዮን ወደ $1.75 ቢልዮን ያሳድጉታል።

በCIP ማሻሽያዎቹ አካል በማድረግ፣ Dr. Starr በተጨማሪ የሚያቀርባቸው፡-

በDowncounty Consortium የከፍተኛ ት/ቤቶች የስፋት/አቅም ችሎታ ጥናት፣ ዲስትሪክቱ በዚያ አካባቢ ለሚኖር ተጨማሪ እድገት በሚዘጋጅበት ወቅት፤

የዲስትሪክቱ Alternative Education Programs (አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች) ከBlair Ewing Center on Avery Road ወደ ሌላ የRockville አካባቢ መዘዋወር፣ የህንፃ መሻሻልና መስፋፋትን ጨምሮ፤

Rock Terrace Schoolን ወደ የቲልደን መንሰራራት/መስፋፋት አካል ወደ ሆነው የTilden Middle School ቦታ ኩታገጥም የማዘዋወር ግንዛቤ፤

ካውንቲው በሼዲ ግሩቭ ሜትሮ ጣብያ አካባቢ በሚያሳየው እድገት መሰረት አስፈላጊ የሆነ የአዲስ የአውቶቡሶች መነሀሪያ/ዲፖ እቅድ ማዘጋጀት፤ እና

በርካታ ከት/ቤቶች ጋር በተናጠል የተያዙ የቦታ ጥበትን ለማቃለል ያተኮሩ ፕሮጀችቶች እና የመማርያ ክፍል ጭማሪ ፕሮጀችቶች እና ባለው ቦታ በሚገባ መጠቀም።

በቀረቡት ማሻሻያዎች ሁለት ህዝባዊ ችሎቶች በሮብ፣ ኖቭ. 12 እና ሀሙስ፣ ኖቭ. 13 ይከናወናሉ፣ እናም በመጨረሻ የቦርድ ድምፅ መስጠት የሚጠበቅበት ሰኞ፣ ኖቭ. 17 ነው።

[በተጨማሪ ይማሩ]

**የዊንተር አየር፡- ከMCPS ጋር ሁልጊዜ ይገናኙ**

የዊንተር አየር እየተቃረበ ነው። በአደገኛ አየር ሁኔታ ምክንያት ት/ቤት ስለሚዘጉባቸው፣ ዘግይተው ስለሚከፈቱበት እና ተማሪዎች አስቀድመው ስለሚለቀቁባቸው ወላጆች የሚማሩባቸው MCPS የተለያዩ መንገዶች ያቀርባል።

- AlertMCPS (MCPS-**ተጠንቀቅ**)
  ከአየር-ጋር-የተያያዙ የአስቸኳይ ሁኔታዎች እና በት/ቤት ስርአት ተፅእኖ በሚያደርጉ ሌሎች አሳሳቢ ክውነቶች ወቅት የቴክስት መልእክቶች ወይም ኢሜይሎች ከMCPS ተቀበሉ። ወላጆች በተለይ የልጆቻቸውን ት/ቤቶች የሚመለከቱ ማስጠንቀቂያዎች ለመቀበል በኮምፒውተር መመዝገብ ይችላሉ።
  [ለAlertMCPS ተመዝገቡ]

- **የMCPS መነሻ ድርገፅ**
  www.montgomeryschoolsmd.org

- **የQuickNotes የኢሜይል ዜና አገልግሎት**
  ተመዝገቡ በwww.mcpsquicknotes.org

- **የMCPS ኬብል (ቲቪ) ቻነሎች**
  Comcast 34፣ Verizon 36 ወይም RCN 89

- **የተዘገበ መረጃ**
  301-279-3673

- MCPSን ጠይቁ
  301-309-6277። ሰራተኞች ከሰኞ እስከ አርብ ከ7:30 a.m. እስከ 5:30 p.m በእንግሊዘኛና ስፓኒሽ ጥሪ ይቀበላሉ።

- Twitter
  http://twitter.com/mcps

- **ያካባቢ ሬድዮና ቲቪ ጣብያዎች**

**የአስቸኳይ ግዜ መገናኛ መረጃዎች በልጅዎ ት/ቤት ማህደር ወቅታዊ መሆኑን እባክዎ ያረጋግጡ።**

[የMCPS አስቸኳይ ሁኔታ መረጃ አቀባበል]

**ለኮሌጅና ለስራ ስኬት ድጋፍ አዲስ ሽርክና**
የMontgomery County **መምህራንና የቢዝነስ መሪዎች ስራ-ቦታ-ላይ ተሞክሮና፣ ከከፍተኛ ት/ቤት ጀምሮ በ**Montgomery College (MC) **እና በ**Universities at Shady Grove (USG) **በኮሌጅ ትምህርታቸው የሚቀጥል በየትምህርታቸው መስክ የለስራ-ዝግጁ ሙያዎች ለተማሪዎች በተከታታይ ለማቅረብ አዲስ** Integrated Experiential Learning Cooperative (**የተቀነባበረ የመማር ተሞክሮአዊ የህብረት ስራ ማህበር**) (IELC) **ለመጀመር ቡድን በመፍጠር ላይ ይገኛሉ።**

**ይህን ተነሳሽነት ለማስጀመር ለማገዝ መነሻ ገንዘብ በ$525,000 የአመራር ስጦታ ከ**Hess Foundation - **በአንዲ እና ቸክ ሄስ ወንድማማቾች፣ በጌይተርስበርግ የ**HESS Construction **ባለቤቶችና መስራቾች የተመራ - እየቀረበ ነው።**

IELC **የተተለመው - ከከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት በኮሌጅ በሞላ - የ**Montgomery County **የትምህርት መስመር ተማሪዎችን በየትምህርታቸው መስክ ወደ የተሞክሮአዊ የመማር ተሞክሮ በተቀነባበረና በገስጋሽ ዘይቤ መዳረሻ ለማቅረብ ነው።** IELC **ተማሪዎችን የአክዴሚያቸውን አስፈለጊነትና ዋጋ እንዲያዩ፣ እናም ስለተጨባጭ የስራ ተጠባቂዎች የበለጠ ግንዛቤ እንዲያተርፉ ያግዛቸዋል።**

**ሶስቱ ትምህርታዊ ሽርኮች** – MCPS፣ MC **እና** USG – **ተሳታፊ ተማሪዎች በትምህርት መንገዳቸድው በሚያዘግሙበት ወቅት፣ እያንዳንዳቸው እርስበራሳቸው ተደጋግፈው የሚገነባቡ የተቀነባበሩ ተሞክሮአዊ የመማር እድሎች ያቀርባሉ።**

**የመጀማሪዎቹ 60 አስራአንደኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ቡድን በሜይ 2015 ይጀመራል እናም** የMCPS፣ MC **እና** USG **የጋራ ተነሳሽነት ከሆነው ከ**ACES (Achieving Collegiate Excellence and Success) **ተሳታፊ ተማሪዎች መካከል ይመረጣሉ።**

[በተጨማሪ ይማሩ]

**በቅርብ ግዜ የሚመጣ፡- ለማመልከቻ ፈተና - ፕሮግራሞች ብቻ** (Testing for Application-Only Programs)

**ማመልከቻ ለማግኘት-ብቻ** (application-only programs) **በ**Montgomery Blair፣ Richard Montgomery **እና** Poolesville **ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ እንዲሁም በ**Roberto Clemente፣ Eastern **እና** Takoma Park **የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፕሮግራሞች የተሟላ ማመልከቻ ላቀረቡ ተማሪዎች ፈተና ቅዳሜ፣ ዲሰ.** 6 **ፕሮግራም ተደርጓል። ለተጨማሪ ዝርዝሮች ማመልከቻውን ተመልከቱ።**

**ለኤሌሜንታሪ** Highly Gifted Centers (**ከፍተኛ ተሰጥኦ ማእከሎች**) **ፈተና በጃኑዋሪ ወር በአካባቢ ት/ቤቶች ይሆናል።**

DCCAPS

Montgomery County Recreation Guide (**የመዝናኛ መመርያ**) **በአሁኑ ወቅት ይገኛል።**

**የዊነተር ወራት ህትመት** Montgomery County Guide for Recreation and Parks Programs (**የመዝናኛና የፓርኮች ፕሮግራም መመርያ**) **በአሁኑ ወቅት ይገኛል። ብዙ ፕሮግራሞች ቶሎ ስለሚሞሉ የ**Montgomery County **ነዋሪዎች ቶሎ እንዲመዘገቡ እናደፋፍራለን። መመሪያው በመቶዎች የሚቆጠሩ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች ያቀፈ ሲሆን የውሃ ተግባራት/እንቅስቃሴ፣ ኪነ ጥበብና የእጅ ስራ፣ ስፖርትና ውዝዋዜ (ዳንስ) ያካትታል።**

**መመርያውን በኮምፒውተር ለማየት** Department of Recreation **ድረገፅ ይጎብኙ። የታተሙ ቅጂዎች በመዝናኛ ማእከሎች፣ በመናፈሻ መገልገያዎች፣ በመንግስታዊ ህንፃዎችና ቤተመፃህፍት ይገኛሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣** 240-777-6840 **ይደውሉ።**

**የዊንተር ኮት/ካፖርት ዘመቻ ተጀምሯል**

**የቅድመሙአለህፃናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራም የአራትና የአምስት አመት ልጆች አዲስ የክረምት ኮቶች ለመስጠት ስጦታዎች በመሻት ላይ ይገኛል።**

**መጠናቸው** 6፣ 6X፣ **እና** 7/8 **የሆኑ ኮቶች እና ሌሎች የዊንተር ልብሶች እንደ ቆቦች/ባርኔጣዎች፣ ጓንቲዎች እና የአንገት ላይ መሀረሞች/ስካርቭ በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ። ስጦታዎችን ወደ** MCPS Prekindergarten/Head Start Program, Rocking Horse Road Center, Room 141, 4910 Macon Road, Rockville, MD 20852, attention: Lisa Conlon **ብላችሁ ላኩ።**

**ለተጨማሪ መረጃ** Lisa Conlon (**ሊዛ ካኖን**) **በ**301-230-0676 **ተገናኙ።**

**ህይወት ዘርቷል! በጀርመንታውን ቤተመፃህፍት Kinetic Art Lab**

**የጀርመንታውን ቤተመፃህፍት ነፃ የSTEM ፕሮግራም ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ቅዳሜ፣ ኖቭ. 15፣ ከ10 a.m. እስከ 12 ቀትር እና ከ12:30 p.m. እስከ 2:30 p.m ያቀርባል። የ"Kinetic Art Lab (ተንቀሳቃሽ ኪነጥበባት ላቦርቷር)ፕሮግራም It's Alive! (ህይወት ዘርቷል!)" ተማሪዎችን በLEDዶች አማካይነት የሚሽከረከሩ፣ ብርሃን የሚሰጡ መለኮታዊ ሀውልቶች (glowing hypnotic kinetic sculptures)፣ ሞተሮችና የእለታዊ ቁሶች ነድፈው እንዲሰሩ እድሎች ይሰጣቸዋል። ሰርክዊቶች እና ቀላል ማሽኖች ተገጣጥመው እንዴት ተወራራሽ የኪነት ስራ እንደሚፈጥሩ ተማሪዎች ይማራሉ።**

**ቤተመፅሀፉ የሚገኘው በጀርመንታውን በ19840 Century Boulevard ነው። ለተጨማሪ መረጃ 240-777-0110 ይደውሉ።**

MCPS **በዜናዎች**

**ጥቂት ትርፍ ደቂቃዎች አለዎትን? እንግዲያስ ስለ**MCPS **ወቅታዊ ርእሰ አንቀፆች፣ ቪድዮዎች እና የጋዜጣ መግለጫዎችን ይከታተሉ።**

***ቪዲዮዎች***

የኮሌጅና የስራ ስኬት ለመደገፍ አዲስ ሽርክና
የMCPS ተማሪዎች አዲስ ህንፃ ነድፈው ይገነባሉ
Superintendent ለት/ቤት ህንፃ ስራ $221 ሚልዮን ጭማሪ ይጠይቃል
የአንድ ቀን ሳይንቲስቶች
Takoma Park MS ብሄራዊ የት/ቤት ምሳ ሳምንት ያከብራል
ይኖቤል ፕራይዝ ተሸላሚዎች በB-CC ተመልካቾች/አዳማጮች ተገረሙ
የሆሎኮስት ተራፊዎች ታሪክን ህይወት ይሰጡታል

***MCPS በዜናዎች***

የWestover ርእሰመምህር የMCPS የልቀት ሽልማት አሸናፊ ሆነ/ች
የParkland Middle School ተማሪዎች የህዋ ሳይንስ ቀጥተኛ ተመልካቾች መሆን ቻሉ
የMontgomery የትምህርት ቦርድ እጩዎች በቦታ ጥበትና በግኝት ክፍተት ላይ ያተኩራሉ
የሜሪለንድ ት/ቤት የቤት ስራ አያስፈልግም ትላለች
Starr የት/ቤት ህንፃ ስራ ገንዘብ በማፈላለግ ላይ ነው
የስቴት ቦርድ የፈተና ለውጦች እንዲዘገይ በድምፅ መስጠት ወሰነ
የMontgomery ት/ቤቶች ዋና ሀላፊ የ$221 ሚልዮን ተጨማሪ የሕንፃ ስራ ገንዘብ ሀሳብ ያቀርባል
የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የ'zombie outbreak' ዘመቻ ለማቆም አገዙ

[የአያትህ/ሽ የሙያ ትምህርት አይደለም]
[የBethesda’s Westbrook Elementary፡- በ75 አመቱ አሁንም ጠንካራ ነው]

***ጋዜጣዊ መግለጫዎች***

[Universities at Shady Grove ከMontgomery College፣ MCPS፣ Business Leaders Experiential Learning Cooperative ለመጀመር ተቀላቀላቸው]
[የትምህርት ቦርድ በኤኮኖምያዊ ትብብርና የእድገት የሙከራ ፈተና ድርጀት ተወያየ፤ በካውንቲ ደንብ አስተያየት ሰጠ]
[Superintendent ለት/ቤት ህንፃ ስራ በጀት የ$220.8 ጭማሪ ይጠይቃል]

---

**ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ድር-ጣቢያ (Blog) የቅርበት ጊዜ መረጃ**
[የስቴት ቦርድ ትክክለኛ ተግባር ፈፀመ]
[በማንሰራራት ላይ የሚገኝ ፈተና]
[የስብሰባ ማጠቃለያ፡- ምዝገባ፣ ማስተር ፕላን፣ ለስራ ዝግጁነት]